አሪት ዘፍጥረት

ት.መ.ማ.

ጽሑፍ፡ በቲም ፈሎስ

ትርጉም፡ በግርማዊ

ዕርግት፡ በአቢይ ደምሴ እና በዮናታን ብርሃኑ

ማስታወሻ -

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀምናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ባመዛኙ ከ1954 ዓ.ም. ዕትም የተወሰዱ መሆናቸውን በአክብሮት ለመግለጽ እንሻለን። ሌላው ዓመተ ምህረቶቹ በሙሉ እንደአውሮፓ አቆጣጠር ናቸው። ሥርዓተ ነጥቦቹን በተመለከተ፥ የመጽሐፍ ቅዱስን አጠቃቀም ለመከተል ሞክረናል። ይሽውም ድርብ - ሰረዝ (፤)፥ ነጠላ - ሰረዝ (፥)፥ ሞረት (፡-) እና ሌሎችንም በአግባቡ ለመጠቀም ጥረት አድርገናል። በስህተት የታለፉ ወይም ካለቦታው የተሸነቆሩ ቢኖሩ በይቅርታ እንድታልፉን እንጠይቃለን። በጥቅሶች መካከል የሚገባውን ነጥብ (፥) በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በሁለት ነጥብ (፡) ስለተተካ፥ «ሉቃ.14፡25-27፥ 33» የሚል ብታገኙ፥ የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 14 ከቁጥር 25 እስከ 27 እና በተጨማሪም ቁጥር 33ን ተመልከት ለማለት መሆኑን እንገልጻለን። ሌሎች አስቸጋሪ ምልክቶችም ቢኖሩ በትዕግሥትና በአስተውሎት ተመልከታችሁ እንድትረዱ ይሁን። ጌታችን እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ በጥናቱ ሁሉ እጅግ ይባርካችሁ።

ተርጓሚው

መግቢያ

የመጀመሪያ ቀን፡-

ይህ ዓለም ከየት መጣ? በእግዚአብሔር የተፈጠረ ነው? ወይስ የተፈጥሮ አዝጋሚ የለውጥ ሂደት (ኢቮሉሽን) ውጤት ነው? ክፉት ወደ ዓለም ውስጥ የገባው ለምንድነው? እውነተኛው አምላክ ማነው? ምንስ ዓይነት አምላክ ነው? እያንዳንዱስ ሰው እንዴት ይድናል? እነዚህ ጥያቄዎች የሰውን ልጅ ለዘመናት ሁሉ ሲያስጨንቁት የነበሩ ጥያቄዎች ናቸው። ለእነዚህ ጥያቄዎች የተለያዩ የሃይማኖት ክፍሎች የየራሳቸውን መልሶች የሰጡበት ቢሆንም፥ ክርስቲያኑ ግን ለጥያቄዎቹ መልስ የሚያገኘው ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ብቻ ነው። ለእነዚህም ሆነ ለሌሎችም የሰው ልጅ አዘውትሮ ለሚያንሳቸው ጥያቄዎች መልሶቻቸው በመጽሐፍ ቅዱስ የተሰጠባቸው ሲሆን፥ በተለይም በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ እናገኛዋለን።

በዚህ የት.መ.ግ. ጥናታችን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ክፍል የሆነውን ዘፍጥረትን እናጠናለን። ዘፍጥረት ሌሎቹን የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት በሙሉ ለመረዳት መሠረት ነው። ዓለም እንዴት እንደተፈጠረ፥ ኃጢአት ወደ ዓለም እንዴት እንደገባ፥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተቋረጠው ግንኙነት እንዴት እንደሚቀጥል፥ የተለያዩ ነገዶች ከየት እንደመጡ፥ ወዘተ. ይገልጻል። እንዲሁም ዘፍጥረት የቀሩትን የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ለመረዳት ቁልፍ ሆኖ እናገኘዋለን። እነዚህ የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝቦች የሆኑት አይሁዶች እነማናቸው? አነሳሳቸውስ እንዴት ነበር? በከነዓን ምድር ላይ ምን መብት አላቸው? በዘፍጥረት ጥናታችን ውስጥ እነዚህ ጥያቄዎች እንዴት እንደተመለሱና ከእኛም በአዲስ ኪዳን ዘመን ከምንኖር ሰዎች ጋር እንዴት እንደሚዛመዱ እናያለን። እንደዚሁም በዚህ እጅግ በከፋው ዓለም ውስጥ እንዴት አድርገን ለእግዚአብሔር በጽድቅ እንደምንኖርና የእግዚአብሔር ወዳጅ የነበረውን አብርሃምን እንደምንመስል የምንማራቸው በርካታ ትምህርቶች በዚሁ መጽሐፍ ውስጥ በተጨማሪ እናገኛለን።

እንደ ብዙዎቹ የትመማ ጥናቶቻችን ሁሉ፥ ይህንንም ትምህርታችንን «ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት» በሚለው ስልት በመመራት እናጠናለን። በዚህ የጥናት ዘዴ ስለ አንድ የምንባብ ክፍል መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚል ለማወቅ አስቀድመን ርዕስ ከመምረጥ በፊት አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል መርጠን ለማስተላለፍ የሚፈልገውን ትምህርት ሁሉ ለመረዳት እንሞክራለን። ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት አትኩሮት፥ በመጀመሪያ ወደ ትርጓሜዎች ከመመልከት ይልቅ፥ መጽሐፍ ቅዱስን ለእራሳችን ለማጥናት እንድንችል ማስቻል ነው። በዚህ በዘፍጥረት ጥናታችን፥ በመጽሐፉ ላይ የተመሠረቱትን የተለያዩ ጥያቄዎች በመመለስ ለተማሪው ተጨማሪ እገዛ ተደርጎለታል።

ይህ ኮርስ ሦስት ዋና ዋና ዓላማዎች አሉት፦

1. ተማሪው የዘፍጥረትን መጽሐፍ ትምህርት በጥልቀት እንዲረዳና ታሪኮቹም እንዴት ከሕይወቱ ጋር እንደሚዛመዱ እንዲያስተውል ግድረግ።

2. ተማሪው አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ፥ በተለይም ታሪካዊ ሥነ-ጽሑፍን ለማጥናት ጥሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዘዴዎችን እንዴት እንደሚጠቀም ማስረዳት። ለዚህ ሲባል ትምህርቱ የተዘጋጀው በመጀመሪያ ተማሪው በሳምንቱ ውስጥ የሚያጠናውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በአጭሩ እንዲዳሰስ ተደርጎ ነው። ሁለተኛ፥ ተማሪው የተጠናው ክፍል ምን እንደሚያስተምር መረዳት ይጀምራል፤ ከዚያም የክፍለ-ትምህርቱን መልእክት በመረዳት ከእራሱ ሕይወት ጋር ያዛምዳል። ሦስተኛ፥ መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈበትን የሥነ-ጽሑፍ ዓይነት ለመለየት ከመብቃቱም፥ በተለይም ታሪካዊ ጽሑፎችን እንዴት ተረድቶ መተርጎም እንደሚችልም ይግራል።

3. ተማሪው በእምነት ጉዞው እንዲያድግ መርዳት። እኛም በዚህ የዘፍጥረት መጽሐፍ ጥናታችን ወቅት አራት ጥያቄዎችን በተደጋጋሚ በማንሳት መልሳቸውን ማሰላሰል ይኖርብናል፦

1. መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? የእግዚአብሔርን ቃል ለማጥናት ስንጀምር መጠየቅ የሚገባን የመጀመሪያው ጥያቄ ይህ ነው። በማንኛውም ጊዜ እግዚአብሔር በአንድ የምንባብ ክፍል ውስጥ ምን እንደሚል ለመማር ስንፈልግ፥ ዛሬ ለእኛ ምን እንደሚል ከመመራመራችን በፊት፥ በመጀመሪያ ቃሉን ሲሰጥ ምን ለማለት እንደፈለገ መረዳት ይኖርብናል። የእግዚአብሔር ቃል ምን እንደሚል ለማወቅ የሚረዱ እንደ ማን? የት? መቼ? የመሳሰሉ በርካታ ጥያቄዎች አሉ።

የእግዚአብሔር ቃል ምን እንደሚል ለመረዳት በምንፈልግበት ጊዜ ሁሉ በአእምሮአችን ውስጥ ሊኖሩ የሚገቡ ሦስት ሌሎች መመሪያዎችም አሉ። በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ስውር ትርጉሞችን መፈለግ የለብንም። እግዚአብሔር እውነትን ከእኛ ደብቆ ትርጉማቸውን በመላምት እንድናገኝ አያስገድደንም። እንዲያውም ፈቃዱን በግልጽ እንድንረዳለት የሚፈልግ አምላክ ነው። እኛ ስንሰብክ፥ ወይም ስናስተምር፥ ወይም ከጓደኞቻችን ጋር ስንነጋገር፥ እንደምናደርገው ሁሉ፥ እግዚአብሔርም ግልጽ ትርጉም ባላቸው ቃላት ይጠቀማል። ስለሆነም የእግዚአብሔርን ቃል እንደ ‹ሰምና ወርቅ› ስውር ትርጉም ያለው አድርጎ መቁጠር ስሕተት ነው። እንዳውም ከዘፍጥረት የምናጠናው ብዙው ትምህርታችን ግልጽ እና ቀላል ይሆንባችሁ ይሆናል። ሆኖም እኛም የምንፈልገው ግልጽና ቀላሎቹን እንጂ ስውር ትርጉሞችን አይደለም።

ሁለተኛ፥ አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከዓውደ-ንባቡ አኳያ ሰፋ አድርገን በማየት መረዳት አለብን። ብዙ የተሳሳቱ ትርጉሞች ከቅዱሳት መጻሕፍት የሚፈልቁት በክፍለ-ምንባቡ፥ በመጽሐፉ፥ ወይም በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ትምህርቶች ሳናጤን ስንቀር ነው። መናፍቅነት በአመዛኙ የሚፈጠረው አንድ ሰው ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ በሚያስተምረው ፈንታ ስለ አንድ ጥቅስ ትርጉም የሚያስበውን በተናጠል ሲያስተምር ነው። ለምሳሌ አንዳንድ ክርስቲያኖች በማርቆስ 16 ትምህርት ሳቢያ መንፈሳዊነታቸውን ለማረጋገጥ መርዘኛ እባቦችን መያዝ እንደሚያስፈልግ ያስተምራሉ። ሰፋ ያለ የመጽሐፍ ቅዱስ ግንዛቤ ግን ይህ በፍጹም የመንፈሳዊነት

ግረጋገጫ እንዳልሆነ ያሳየናል። ስለሆነም በዘፍጥረት ጥናታችን፥ በመጀመሪያው ትምህርታችን የመጽሐፉን ጭብጥ ለማግኘት መጽሐፉን በሙሉ እናነበዋለን። ከዚያም በእያንዳንዱ ሳምንታዊ ትምህርት መጀመሪያ፥ በአሳብ እጅግ የተቀራረበውን የመጽሐፉን አንድ ክፍል እናነባለን፤ በዚህም ዓይነት ሳምንቱን ሁሉ የምናጠናውን ንዑስ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በተሻለ ሁኔታ እንረዳለን።

ሦስተኛ፥ በምናጠናው የምንባብ ክፍል ውስጥ የሚገኘውን የሥነ-ጽሑፍ ዓይነት ልብ ማለት አለብን። ምንም እንኳ መጽሐፍ ቅዱሱ የእግዚአብሔር ቃል ቢሆንም፥ እግዚአብሔር ሰብዓዊ ሰዎችን እንደ ጸሐፊነት ተጠቅሞባቸዋል። ሰዎች ሲጽፉ የተለያዩ የሥነ ጽሑፍ ዓይነቶችን ተጠቅመዋል። ዛሬ በዓለማችን የተስፋፉትን የተለያዩ የሥነ-ጽሑፍ ወይም የንግግር ዓይነቶች በዘልማድ ተረድተን በተለየ መንገድ እንተረጉማቸዋለን። መጽሐፍ ቅዱሳችንንም በዚህ መንገድ መተርጎም አለብን።

1ኛ ጥያቄ፤ በኢትዮጵያ የሚገኙትን የሥነ-ጽሑፍ ዓይነቶች ዘርዝር።

በዕለት ኑሮአችን የሚያጋጥሙንን ቀላል ዓረፍተ-ነገሮች «ሰምና ወርቅ»ን ከምንረዳበት በተለየ መንገድ እንተረጉማቸዋለን። ወይም ምሳሌዎችንና ተረቶችን ከግጥም በተለየ ሁኔታ ነው የምንተረጉማቸው። ይህ በመጽሐፍ ቅዱስም እውነት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስት አራት ዋና ዋና የሥነ-ጽሑፍ ዓይነቶችን እናገኛለን፡-

1. በዜና መዋዕል መልክ ወይንም በታሪካዊ ዘገባ የቀረቡ አሉ። ይህም ማለት አንዳንዶቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በትምህርት ቤት እንደምናነበው፥ የታሪክ መጽሐፍ ናቸው ማለት ነው። ሆኖም መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ የሚያደርገው ምክንያት አለ። ባብዛኛው ጸሐፊው ታሪክን የሚጽፈው ከእግዚአብሔር አንጻር ሲሆን፥ የሚጽፈውም ስለ እግዚአብሔር አንድን ግልጽ እውነት ለማሳወቅ፥ ስለ ፈቃዱ ለማስተማር፥ ወይም ፍርድን ሳይቀበሉ እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝ መንገድ እንዴት መመላለስ እንደሚቻል ለማስጠንቀቅ ነው። ዘፍጥረት የታሪካዊ ሥነ-ጽሑፍ ምሳሌ ነው።

2. ግጥምና ቅኔም አለ። መዝሙረ ዳዊትና መጽሐፈ ምሳሌ ለግጥምና ቅኔ ጥሩ ምሳሌዎች ናቸው። በግጥም ብዙውን ጊዜ ጸሐፊው የአነጋገር ፈሊጦችን በመጠቀም መልእክቱን ያስተላልፋል።

3. ትንቢታዊ ጽሑፎች አሉ። ብዙውን ጊዜ ከግጥም ጋር የተያያዙ ቢሆኑም፥ እንደ ዳንኤል፥ ኤርምያስና ራእይ ያሉት ትንቢታዊ ጽሑፎች ትንሽ ለየት ባለ መንገድ መረዳት የሚያሻቸው ናቸው።

4. እንደ ሮሜ እና 1ኛ ጴጥሮስ፥ ወዘተ. መጻሕፍት ለግለሰቦች ወይም ለአብያተ ክርስቲያናት የተጻፉ ደብዳቤዎች አሉ። እያንዳንዱ ሥነ-ጽሑፍ በራሱ ዘይቤ መተርጎም አለበት። የዘፍጥረት መጽሐፍ ሦስት ዓይነት ሥነ-ጽሑፎችን አካትቶ ይዟል። አብዛኞቹ ክፍሎች ስለ እግዚአብሔር፥ ስለ እስራኤል፥ ወዘተ. አንዳንድ እውነታዎችን ለማስተማር በታሪካዊ ዘገባ መልክ የቀረቡ ቢሆንም፥ በግጥምና በትንቢት መልክ የቀረቡ መጠነኛ ክፍሎችም አሉት።

ብዙውን ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ-ነክ ጽሑፎችን ስናነብ ትኩረታችን ጸሐፊው በሚነገረን የቀድሞ ታሪክ ወይንም ትረካ ላይ ብቻ ይሆናል። የቀድሞ ታሪክን ወይም ትረካውን ማወቅ ቢኖርብንም፥ ከታሪኩ በስተጀርባ ያለውን ዋና መልእክት ማጤንም አለብን። በዘፍጥረት ሙሴ ለእስራኤላውያን ታሪካቸውን ለማስተማር ቢፈልግም፥ ሌላ ዓላማም ነበረው። ሊጽፋቸው ይችል የነበሩ ሌሎች ብዙ ታሪኮች ቢኖሩትም ቅሉ፥ ሕዝቡን የተሻለ ትምህርት የሚያስተምሩትን መረጠ። የአብርሃም ታሪኮች ለእስራኤላውያንና ዛሬም ለእኛ የእምነት ኑሮ ምን እንደሚመስል፥ ሽልማቶቹ ምን እንደሆኑ፥ መሰናክሎቹንም ለማስተማር የተጻፉ ናቸው። ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮችን ስናነብ፥ የታሪክ መጻሕፍትም ይሁኑ (ከዘፍጥረት እስከ ነህምያ)፥ ወይም በወንጌላት ውስጥ፥ ከሕይወታችን ጋር የምናዛምዳቸውን ትምህርቶች መፈለግ አለብን። እነዚህ ትምህርቶች ብዙውን ጊዜ በታሪኩ ውስጥ በተጠቀሱ ገጸ-ባሕርያት፥ ድርጊቶችና አመለካከቶች ውስጥ የሚታዩ ናቸው።

2. «መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?» የሚለውን ከጠየቅን በኋላ መጠየቅ የሚኖርብን ሁለተኛው ዓይነት ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ማለቱ

ነው? የሚለውን ይሆናል። በዚህ በሁለተኛ ደረጃ ትርጉማችን ደራሲው የሚሰጠውን ትርጉም ጠለቅ ብለን እናያለን። ለምሳሌ እንደ ጸጋና ሰላም ያሉትን ቃላት ትርጉም ጠለቅ ብለን መመራመር እንጀምራለን፤ ወይም ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸውን ቀደምት መረጃዎችን እንሰበስባለን። ጸሐፊው የሚያስተምራቸውን ዋና ዋና ትምህርቶች በጥልቅ መመልከት እንጀምራለን። ምናልባት እዚህ ላይ ማንሳት የሚያስፈልገን ዋና ጥያቄ ለምን? ወይም ምን ማለቱ ነው? የሚል ይሆናል። ይህ ከመጀመሪያው የትርጉም ደረጃ በጥብቅ የተያያዘ ቢሆንም፥ የበለጠ ጥልቀት አለው። ነገር ግን ይህን ደረጃ ካልጠበቅን፥ ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ስለሚያስተምረው ነገር የተሳሳተ ግንዛቤ ሊኖረን ይችላል።

3. ይህ ለእኔ ወይም ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጠው ትርጉም ምንድን ነው? የሦስተኛው ደረጃ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ደረጃ ላይ ይታነጻል። እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ወይም ለቀደምት ክርስቲያኖች የተናገረው ምን እንደሆነ ሲገባን ብቻ ነው፥ ዛሬ እግዚአብሔር ምን እንድናውቅ ወይም እንድንሠራ እንደሚፈልግ የምንገነዘበው። እርግጥ ከዛሬው ሕይወታችን ጋር በቀጥታ የማይዛመዱ በርካታ ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አሉ። እነዚህ በጸሐፊው ዘመን ለኖሩ ሰዎች የተሰጡ ትዕዛዛት ወይም ሕግጋት ነበሩ። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ሁል ጊዜ ልናውቃቸውና ከዘመናችን ጋር ልናዛምዳቸው የምንችላቸውን መመሪያዎች የያዘ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ተማሪዎች እንደመሆናችን መጠን፥ እነዚህ መመሪያዎች ምን እንደሆኑ ተረድተን፥ በትክክል ከሕይወታችን ጋር ልናዛምዳቸው ይገባል። በዘፍጥረት ጥናታችን ውስጥ፥ ይህ ትምህርት ዛሬ ለእኛ ምን ትርጉም አለው? ለቤተ ክርስቲያንስ? የሚሉትን ጥያቄዎች ስንመልስ፥ ይህን ለማድረግ እየሞከርን ነው ማለት ነው።

4. እግዚአብሔርን በመታዘዝ እኔ ምን ማድረግ አለብኝ? የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ ብቻ ሳይሆን፥ መታዘዝም ያሻል። የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ካላወቅን፥ መታዘዝ አንችልም። ነገር ግን አንዴ ካወቅነው፥ መታዘዝ አለብን። ስለዚህ

የእግዚአብሔርን ቃል ስናጠና ራሳችንን ሁል ጊዜ ምን ላድርግ? እንዴት ራሴን ልለውጥ? እግዚአብሔር የሚያስተምረኝን ለመታዘዝ ምን ተግባር ልፈጽም? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል።

2ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) መጽሐፍ ቅዱስን በምናጠናበት ጊዜ መጠየቅ ያለብንን አራት ጥያቄዎች ዘርዝር።

ለ) ዮሐ. 3፡16 ተመልከት። «ምን ይላል?» የሚለውን ጥያቄ መልስ ለመረዳት የሚያግዝህን አንድ ጥያቄ ጻፍ።

ሐ) «ምንስ ማለት ነው?» የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ የሚያስችል አንድ ጥያቄ ጻፍና መልሱን ስጥ።

መ) «ለእኔስ ምን ይላል?» ለሚለው ጥያቄ አንድ መልስ ስጥ።
ሠ) «ምን ማድረግ አለብኝ?» ለሚለው ጥያቄ አንድ መልስ ስጥ።

ይህን መጽሐፍ በምታጠናበት ጊዜ፥ በጥናት መመሪያው ውስጥ የተጻፈውን በማስተዋል አንብብ። ጥያቄዎችን በጥንቃቄ አስበህ መልስ። የእግዚአብሔርን ቃል በግላችን ማጥናት መማር አስፈላጊ ነው። ይህን የምናደርገው አስፈላጊ ጥያቄዎችን እንዴት እንደምንጠይቅ በመማርና የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረውን ሁሉ በማስተዋል ነው። ስለዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎችን ድጋፍ ከመፈለግህ በፊት፥ እነዚህን ጥያቄዎች መመለስህን፥ በምንባቡ ላይ ጊዜ ወስደህ ማሰብህንና ማሰላሰልህን አረጋግጥ። ምናልባት የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜዎች ያልጠቀሷቸው አንዳንድ ፍሬ ነገሮች ያጋጥሙህ ይሆናል። ማስታወስ ያለብህ ትርጓሜው አንዱ ሰው ከእግዚአብሔር ቃል የተረዳው ትርጉም ብቻ መሆኑን ነው። መልሶችን ከመስጠትህ በፊት በጥልቅ ልታሰብባቸው ከመገባቱም፥ አብረን የምናጠናውን ትምህርት ከሕይወትህ ጋር ለማዛመድ ሞክር። የእግዚአብሔርን ቃል ማጥናት ብቻ ሳይሆን፥ መታዘዝም አለብህ። ሮሜ 15፡4 «በመጽናትና መጻሕፍት በሚሰጡት መጽናናት ተስፋ ይሆንልን ዘንድ አስቀድሞ የተጻፈው ሁሉ ለትምህርታችን ተጽፎአልና» ይላል።

ይህ መጽሐፍ የተጻፈው እንደ ጥናታዊ መጽሐፍ እንዲያገለግል ብቻ ሳይሆን፥ ለመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜም እንዲያገለግል ጭምር ነው። ዘፍጥረትን በምታጠናበት፥ ወይም በምታስተምርበት ጊዜ ሁሉ ይህን መጽሐፍ እንደግጣቀሻ ልትጠቀምበት ትችላለህ።

የጥያቄዎቹን መልሶች በደብተርህ ላይ ጻፍ። የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት ከሌለህ በጥናትህ እንዲረዳህ አንድ ለማግኘት ሞክር። ከቻልህ ደግሞ ከዚህ ትምህርት ጎን ለጎን፥ እንደ ዘፍጥረት ትርጓሜ ያለ ተጨማሪ የትርጓሜ መጽሐፍ ብታጠና የበለጠ ይረዳሃል። አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉምም ካለህ ከዚያም እንዲሁ አንብብ።

ተግሪውን በጥናቱ ለመርዳት ሲባል ትምህርቶቹ በአምስት ቀናት ተከፍለዋል። የየቀኑን ትምህርት በአንድ ጊዜ ለመጨረስ ሞክር። አንዳንድ ትምህርቶች ከሌሎቹ በላይ ረጃጅም ስለሆኑ፥ በቂ ጊዜ መድበህ ከሳምንቱ ሰብሰባ በፊት መጨረስ መቻልህን አረጋግጥ። ትምህርቶቹ ብዙ ተዘግጅ ጥቅሶች አሏቸው። «ተመልከት» የሚሉትን ለመመልከትህ እርግጠኛ ሁን። «ተመልከት» የማይሉትን ግን፥ በቂ ጊዜ ካለህ ልታጠናቸው ትችላለህ፤ ወይም ሌላ ጊዜ ትመለስባቸዋለህ።

ትምህርት አንድ

3ኛ ጥያቄ፤ - የአገራችንን፥ የቤተ ክርስቲያናችንን፥ የነገዳችንን፥ ወዘተ. ታሪክ ማወቅ ያለብን ለምንድነው?

በብዙ መንገዶች የቀድሞ ታሪካችን የዛሬ ማንነታችንን ይወስናል። ሁላችንም በኢትዮጵያ ውስጥ ተወልደን አድገናል። ኢትዮጵያ በምድር ላይ ካሉት ከሌሎች አገሮች ሁሉ የተለየ ባህል፥ ቅርስና ታሪክ ያላት አገር ነች። ይህ ኢትዮጵያን እንደ አገር የተለየች ያደርጋታል፤ በእኛም ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ታሪካችንን ባጠናን ቁጥር፥ ራሳችንን በበለጠ እያወቅን እንመጣለን። የዘፍጥረት መጽሐፍ ወደ ታሪክ መጀመሪያ መልሶ ይወስደናል። ይህም የራሳችንን ማንነት እንድንገነዘብ ይረዳናል። ሰዎች በመሆናችን በአምላክ አምሳል የተፈጠርን የፍጥረት ቁንጮዎች ነን። ስለዚህ የሰው ሕይወት ሁሉ ክቡር ሆኖ መታየት አለበት። ይሁን እንጂ በዘፍጥረት ሰው እንዴት በታላቅ ክፋት ወድቆ የእግዚአብሔርን

አምሳል እንዳበላሸ እንመለከታለን። ይህም ሁላችንም ምንም ያህል መልካም ለማድረግ ብንጥርም፥ ለምን ክፉ ነገር የመሥራት ዝንባሌ እንዳለን ያሳየናል። የዘፍጥረት መጽሐፍ፥ እግዚአብሔር በሰው ሕይወት ውስጥ የተበላሸውን አምሳሉን እንደገና ለማበጀት እንዴት እንደሚሠራ ማሳየት ይጀምራል። እንዲሁም በዓለም ላይ ይህን ያህል በርካታ ጦርነትና ክፋት ለምን እንደሚታይም ከዘፍጥረት እንመለከታለን። ለዚህም ሁሉ ዘፍጥረት ተጠያቂ የሚያደርገው እግዚአብሔርን ሳይሆን፥ ኃጢአተኛውን ሰው ነው።

ዘፍጥረት የኢትዮጵያ ሕዝቦች ሕልውና ከማግኘታቸው ከረጅም ጊዜያት በፊት ስለ ነበረው የዘመንና የሕዝቦች ጅማሬ የሚናገር መጽሐፍ ነው። ለእስራኤላውያን ግን ዘፍጥረት ሌላ ተጨማሪ ትርጉምም አለው። የብሉይ ኪዳን ዋና ትኩረት በኢትዮጵያ፥ በአሜሪካ፥ ወይም በአውሮፓ ላይ አይደለም። የብሉይ ኪዳን ትኩረት አነስተኛ ቁጥር ባለው የአይሁድ ሕዝብ ላይ ነው። አብዛኛው የዘፍጥረት ክፍል፥ የእስራኤልን ሕዝብ ጅማሬ የሚተርክ ነው።

ምናልባት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የዘፍጥረትን ያህል ክርስቲያን ባልሆኑ ሰዎች ተቃውሞ የደረሰበት መጽሐፍ አይኖርም። ሳይንቲስቶች እግዚአብሔር ዓለምን መፍጠሩን ይቃወማሉ። ይልቁንም የምንኖርባት ዓለም የፍንዳታና የአዝጋሚ ለውጥ ሂደት ዕድገት ውጤት ነች ብሎ ማመኑ ይቀናቸዋል። ብዙዎቹ ዘፍጥረትን ሰዎች ስላለፈው ታሪካቸው እንደሚናገሩት ተረት አድርገው ይቆጥሩታል። ዘፍጥረት ስለ ሰው አመጣጥ በአባቶች አፈ-ታሪክ የተሞላ እውነት ያልሆነ የፍጥረት ተረታ-ተረት ነው ይላሉ።

4ኛ ጥያቄ፤ - የማያምኑ ሰዎች እግዚአብሔር፥ ወይም ዘላለማዊ ፍርድ የለም ብለው የሚከዱት ለምን ይመስልሃል?

ፈጣሪ አምላክ ከሌለ፥ ሰው በምግባሩ ለማንም ተጠያቂ አይሆንምና ዘላለማዊውም ፍርድ አይኖርም። ስለዚህ ሰዎች በዘፍጥረት የፍጥረት ታሪክ የማያምኑበት ምክንያት፥ ይህን ካደረጉ በእግዚአብሔር ማመን ስለሚኖርባቸው ነው። እግዚአብሔር የለም ብለው ከካዱ ግን፥ በፈጣሪያቸው ዘንድ ተጠያቂ አይሆኑም። እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ

ምንም ሥልጣን ስለሌለው፥ እንዳሻቸው ሆነው ለመኖር ይችላሉ። ለኃጢአቶች ሁሉ መሠረቱ፥ እግዚአብሔርን፥ ፍጥረቱን (እኛንም) በውሳኔዎቻችን ላይ ማዕከለኛውና ወሳኙ ነጥብ እራሳችንን አድርገን ለመተካት የምናደረገው ሙከራ ነው።

5ኛ ጥያቄ፤ - በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ስንሠራ፥ ይህ እንዴት እውን ይሆናል?

የታሪክ ምሑራንም በበኩላቸው የመጽሐፍ ቅዱስን ታሪክ፥ በተለይም በዘፍጥረት ውስጥ የሚገኘውን ይቃወማሉ። ከመጀመሪያው ሰው አንስቶ በዘፍጥረት እስከተገለጸው የሰለጠነ ሰው ድረስ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዓመታት አልፈዋል ይላሉ።

ይበልጥ የሚያሳዝነው፥ ክርስቲያን የሥነ-መለኮት ጠበብት ተብዬዎቹም ደግሞ የዘፍጥረትን መጽሐፍ መቃወማቸው ነው። አንዳንዶች ከዘመናዊው ሳይንስና ታሪክ ጋር ለማስማማት ሲሉ ዘፍጥረትን ለልጆቻችን እንደምንነግራቸው ተረቶች ዓይነት፥ ግብረ-ገብነትን ለማስተማሪያ ከሚጠቅሙ መጻሕፍት ወገን ይመደባል እንጂ እውነትነት የለውም ይላሉ።

6ኛ ጥያቄ፤ - መጽሐፍ ቅዱስን በዚህ መልክ ማየቱ አደገኛ የሚሆነው ለምንድነው?

ለክርስቲያን በዘፍጥረት ትክክለኛነት ማመኑ አስፈላጊ ነው። አለዚያ ክርስቲያን ዓለም እንዴት እንደተፈጠረች፥ ወይም ክፋት እንዴት እንደተጀመረ፥ ወይም ሰውን የሚወድ አንድ ሃያል አምላክ እንዳለ አያውቅምና ተስፋ የለውም ማለት ነው። በዘፍጥረት ትክክለኛነት ካላመንን፥ በማንኛውም የእግዚአብሔር ቃል እምነት ሊኖረን ቀርቶ፥ ኢየሱስ እንኳ ለእኛ እንደሞተ ልንቀበል አንችልም። ጳውሎስ በ2ኛ ጢሞቴዎስ 3፡16 በመንፈስ ቅዱስ ምሪት (2ኛ ጴጥሮስ 1፡20-21)፥ «የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ» ይላል። በሌላ አባባል፥ ዘፍጥረትን ጨምሮ ለመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በሙሉ ምንጩ እግዚአብሔር ስለሆነ፥ እግዚአብሔር እውነተኛ እንደሆነ እውነተኞች ናቸው። ኢየሱስ ስለ ብሉይ ኪዳን ሲናገር፥ «እውነት፥ እውነት እላችኋለሁ፤ ሰማይና ምድር እስኪያልፉ ድረስ ከሕግ አንዲት የውጣ

ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም» (ማቴ. 5፡18) ብሎ ነበር። ክርስቲያኖች እንደመሆናችን፥ የምንይዛቸው እምነቶች፥ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ፥ በቀድሞ ጊዜ የተፈጸሙትን ክስተቶች በትክክል እንደሚገልጽና በውስጡ በሚገኘው የደኅንነት መልእክት ላይ ባለን እርግጠኛነት ላይ የተመረኮዙ ናቸው። የመጽሐፍ ቅዱስን ትክክለኛነት በማንኛውም ነጥብ ላይ መጠራጠር ከጀመርን፥ የእምነታችን መሠረት ይናጋና ወዲያው ባለማመን ውስጥ እንወድቃለን።

ዘፍጥረት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ሥፍራ

በዚህ ሳምንት ውስጥ፥ መጽሐፉ የሚያስተምረውን ጭብጥ ለማግኘት የዘፍጥረትን መጽሐፍ ገረፍ ገረፍ አድርገን እናነባለን። በምታነብበት ጊዜ ዋና ዋና ክስተቶችንና የሚገኙባቸውንም ምዕራፎች በመዘርዘር አስተዋጽኦ አውጣ። (ለምሳሌ ዘፍጥረት 1-2 - የዓለም ፍጥረት፥ ወዘተ.)።

7ኛ ጥያቄ፤ - ዘፍጥረት 1-11 አንብበህ፥ በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙትን ዋና ዋና ክስተቶች ዘርዝር።

ዘፍጥረት የመጀመሪያው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ነው። በመሆኑም የመጽሐፍ ቅዱስን የመጀመሪያ ክፍል ከሚመሠርቱት ከአምስቱ መጻሕፍት አንዱ ነው። ይህ ክፍል በብዙ የተለያዩ ስሞች ሲጠራ ቆይቷል። አንዳንዶች ‹አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት› ወይም ‹አምስቱ የሕግ መጻሕፍት› ሲሉት፥ ሌሎች ድግሞ ‹ፔንታቱክ› ይሉታል። ፔንታቱክ የግሪክ ቃል ሲሆን፥ ትርጉሙም ‹አምስት› ማለት ነው። ፔንታቱክ ማለትም የመጀመሪያዎቹ አምስቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ማለት ሲሆን፥ ጸሐፊውም ሙሴ ነው ተብሎ ይነገራል።

8ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) አንዱን ግዕዝ የሚያውቅ የኦርቶዶክስ ቄስ፥ ኦሪት ዘፍጥረት፥ ዘጸአት፥ ዘሌዋውያን፥ ዘኍልቁና ዘዳግም በግዕዝ ምን ማለት እንደሆነ ጠይቅ።

ለ) ዘፍጥረት የሚለው ቃል፥ የዘፍጥረትን መጽሐፍ እንዴት ይገልጻል?

9ኛ ጥያቄ፤ ሌሎቹን አራት የፔንታቱክ መጻሕፍት ዘርዝር። እያንዳንዱ መጽሐፍ ስለምን እንደሚናገር ባጭሩ ግለጽ።

በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የዘፍጥረት ርዕስ ሁለት ስሞችን ይዞአል። በመጀመሪያ «ኦሪት» የሚል ስም ተሰጥቶት እናገኛለን። የኦርቶዶክስ ቁሶችን ጨምሮ፥ ብዙ ሰዎች ይህ ቃል ምን እንደሆነ አያውቁም። ለመጀመሪያ አምስቱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ብቻ የተሰጠ ስም ነው። ‹ሕግ› ማለት ሳይሆን አይቀርም። ሁለተኛ፥ ‹ዘፍጥረት› የሚለው የግዕዙ ስም በአማርኛው ‹መፍጠር› እንደ ማለት ነው። በሌላ አባባል የዘፍጥረት መጽሐፍ ስለ ዓለም ጅማሬ፥ ወይም ስለ ፍጥረት የሚናገር መጽሐፍ ነው። የዚህ መጽሐፍ ስያሜ ምንጩ እግዚአብሔር ዓለምን እንዴት እንደፈጠረ ከሚተርኩት ከሁለቱ የመጀመሪያ ምዕራፎች የተወሰደ ነው። ነገር ግን «ጀነሲስ» የሚለው የእንግሊዝኛው ቃል ‹ጅማሬዎች› የሚለውን ቃል የበለጠ ይገልጻዋል። ጀነሲስ የፍጥረትን ሁሉ ጅማሬ ይገልጻል። እንደዚሁም ደግሞ የኃጢአትን፥ የሕዝቦችን፥ መሥዋዕት በማቅረብ የሚገኘውን የደኅንነት መንገድና የሕዝበ-እስራኤልንም ጅማሬ ይናገራል።

ዘፍጥረት ስለ ነገሮች ጅማሬ ስለሚናገር፥ በቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፥ ስለ እነዚህ ነገሮች ላሉን ግንዛቤ መሠረት ይጥልልናል። ፈጣሪ፥ አዳኝና የአብርሃም አምላክ ስለሆነው እግዚአብሔር ያስተምረናል። ሰው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረውን ጤናማ ግንኙነት ስላበላሸው ስለ መጀመሪያው ኃጢአትም እንማራለን። የእስራኤል ሕዝብ እንዴት እንደተመሠረተም እንረዳለን። የቀረው የብሉይ ኪዳን ክፍል የሚያተኩረው የእስራኤል ሕዝብና የእግዚአብሔር ምርጥ ስለሆኑት አይሁዶች ስለሆነ፥ የሕዝበ እስራኤል ጅማሬ እንዴት እንደነበረና ለምንስ እንደተመረጠ ማወቅ ያሻናል።

10ኛ ጥያቄ፤ - ኢሳ. 42፡6 ተመልከት። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለምን መረጣቸው?

የዘፍጥረት መጽሐፍ ታሪክ ከቀሩት የፔንታቱክ ታሪኮች ጋር የተያያዘ ነው። በዘፍጥረት የእስራኤልን ሕዝብ ጅማሬ እናገኛለን። በእርግጥ የመጽሐፉ አብዛኛው ክፍል የእስራኤላውያንን የዘር ሐረግ ያሳያል።

የእስራኤልን የዘር ሐረግ ከአዳም እስከ ሴት፥ ኖኅ፥ ሴም፥ ታራ፥ በመጨረሻም እስከ አብርሃም ያሳያል። የመጽሐፉ ክፍል በአመዛኙ ስለ መጀመሪያው የአይሁድ ቤተሰብ፥ አብርሃም፥ ይናገርና ቤተሰቡ እንዴት ወደ ይስሐቅ፥ ያዕቆብ፥ ከዚያም እንዴት ወደ አሥራ ሁለቱ የእስራኤል መሥራች አባቶች እንዳደገ ይገልጻል። የዘፍጥረት መጽሐፍ እስራኤላውያን ከነዓንን የመውረስ ተስፋ ቢሰጣቸውም እንዴት በግብጽ ባርነት ሥር እንደኖሩ በመግለጽ ያበቃል። እንዲሁም ዘፍጥረት፥ ለአብርሃም የተሰጡት የእግዚአብሔር የተስፋ ቃላት ለእስራኤል ሕዝብ እንዴት ከትውልድ-ወደ ትውልድ እንደተላለፉላቸው ያሳያል።

ከዘፍጥረት የሚቀጥለው መጽሐፍ ዘጸአት ሲሆን፥ የስሙ ትርጉም በግዕዝ ‹መውጣት› ማለት ነው። የሚገልጸውም እስራኤላውያን ከባርነት ቀንበር ተላቅቀው ወደ ሲና ተራራ እንዴት እንደ ተጓዙ ነው። አብዛኛው የዘጸአትና የዘሌዋውያን ክፍል (የእስራኤል የክህነት ነገድ ስለሆኑት ሌዋውያን የሚናገር) በእግዚአብሔርና በእስራኤል መካከል በተደረገው ቃል ኪዳን ላይ ያተኩራል። በግዕዝ ዘጎልቅ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሚያውቁት ሰዎች እጅግ ጥቂት ናቸው። ከአርባ ዓመታት መንከራተት በኋላ እስራኤላውያን እንዴት ወደ ተስፋዱቱ ምድር ድንበር እንደደረሱ ይተርካል። ዘዳግም የሚለው ቃል ትርጉም ‹መድገም› ወይም ‹እንደገና መስጠት› ሲሆን፥ ሙሴ ከመሞቱ አስቀድሞ፥ ከእግዚአብሔር ጋር በተደረገው ቃል ኪዳን ውስጥ የሚገኙትን ሕግጋት ለእስራኤል ሕዝብ እንደገና ያስታወሰበት መጽሐፍ ነው።

ዘፍጥረት ከዮሐንስ ራእይ መጽሐፍም ጋር ይዛመዳል። ዘፍጥረት የእግዚአብሔር የዘለዓለሙ እቅድ ታሪክ መጀመሪያ ነው። እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረና ዓለሙም እንዴት በኃጢአት እንደተበላሸ ይነግረናል። የተቀረው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እግዚአብሔር ዓለምን በመጀመሪያ በእስራኤላውያን አማካኝነት፥ በመጨረሻም በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ ከራሱ ጋር ለማስታረቅ የነበረውን እቅድ ይነግረናል። የራእይ መጽሐፍም እግዚአብሔር በፍጥረት መጀመሪያ አቅዶት የነበረውን እንዴት እንደሚፈጽም ያሳያል። ኃጢአት ተደምስሶ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ይታረቃል።

ፍጹም በሆነው ኃጢአት-አልባ አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር፥ ሰውና እግዚአብሔር፥ ኃጢአት በሌለበት ግልጽ ኅብረት እየተደሰቱ፥ ለዘላለም ይኖራሉ። የራእይ ጸሐፊ መንግሥተ ሰማይን የሚገልጸው፥ ዔደን ገነት በዘፍጥረት ከተገለጸችበት ሁኔታ ጋር በሚመስሉ በርካታ መንገዶች ነው።

11ኛ ጥያቄ፤ - የእግዚአብሔር ልጆች ለሆንን ለእኛ ይህ እንዴት ታላቅ ተስፋ ይሆናል?

ሁለተኛ ቀን፡ - ጸሐፊው

12ኛ ጥያቄ፤ - ከዘፍጥረት 12-23 አንብብ። ለዘፍጥረት አስተዋጽኦ ጽሑፍ ማውጣትህን ቀጥል። በዚህ ክፍል ውስት የተጠቀሱትን ዋና ዋና ሰዎችና ክስተቶች ዘርዝር።

13ኛ ጥያቄ፤ - የሚከተልቱን ጥቅሶች በማየት ቢያንስ ከፔንታቱክ አንዳንድ ክፍሎችን ማን እንደጻፋቸው ግለጽ፡- ዘጸአት 17፡14፤ 24፡4፤ ዘኁልቁ 33፡1-2 እና ኢያሱ 8፡31-32።

እስካለፈው ምዕተ-ዓመት ድረስ፥ ክርስቲያኖች ሁሉ ሙሴ የዘፍጥረት መጽሐፍ ጸሐፊ እንደነበረ ያምኑ ነበር። የዘፍጥረት መጽሐፍ ግን እንደ ጻፈው አይናገርም። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንዶቹን የፔንታቱክ መጻሕፍት ሙሴ እንደጻፋቸው ይናገራል። ኢየሱስም ሙሴ የፔንታቱክን መጻሕፍት፥ በተለይም ዘጸአትን እንደ ጻፈ ተናግሯል (ማር. 12፡26)።

ዳሩ ግን በቅርቡ ሊቃውንት የሙሴን መጻፍ መጠራጠር ጀምረዋል። የተለያዩ የዘፍጥረት ክፍሎችን፥ ሦስት ወይም አራት የተለያዩ ሰዎች እንደጻፏቸው ይናገራሉ። አሁን ዘፍጥረት ብለን የምናውቀውን መጽሐፍ፥ ከሙሴ ሞት በኋላ ብዙ ቆይቶ አንድ ያልታወቀ ሰው የተለያዩትን ክፍሎች አቀናጅቶ እንደጻፋቸውም ይከራከራሉ።

ሆኖም አብዛኛውን የዘፍጥረት ክፍል ሙሴ አልጻፈም ብለን የምንጠራጠርበት ምክንያት አይኖርም። ዘፍጥረት የተጻፈው በ1440 ዓ.ዓ. ሲሆን፥ ጸሐፊውም ሙሴ ሳይሆን እንደማይቀር ይታመናል።

ሆኖም ወደ በኋላ እንደምንመለከተው፥ አንዳንድ አቀናባሪዎች ከሙሴ ዘመን ከብዙ ዓመታት በኋላ ለነበሩት አይሁዳውያን መግለጫ የሚሆኑ አጫጭር ማብራሪያዎችን ጨምረዋል።

14ኛ ጥያቄ፤ - ዘጸአት 2፡1-10፤ የሐዋ. 7፡20-22 አንብብ። ሙሴ ዘፍጥረትን ለመጻፍ ብቁ የሆነው እንዴት ነበር?

ሙሴ በግብጽ የባርነት አገር፥ ከሌዊ ነገድ የተወለደ አይሁዳዊ ነበር። እንደ አብዛኛዎቹ አይሁዳውያን ልጆች ሙሴም መገደል ቢኖርበትም እንኳ፥ በእግዚአብሔር እቅድና ጥበቃ ከሞት ተረፈ። በፈርዖን ሴት ልጅ እንክብካቤ እየተደረገለት በግብፅ ቤተ-መንግሥት ውስጥ አደገ። በዚያም የግብፃውያንን ባህልና ትምህርት ሁሉ ተማረ። ግብፃውያን በጥንቱ ዓለም በጣም የተራቀቁና የሰለጠኑ ሕዝቦች ነበሩ። ዛሬም እንኳ በሙሴ ዘመን አካባቢ የተሠሩ የግብፅ ፒራሚዶች ሰዎችን እያስደነቁ ናቸው። ሙሴ በጊዜው በነበሩት ምርጥ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ማንበብና መጻፍ ተማረ። በእውነቱ በፔንታቱክ ጽሑፉ ውስጥ ይህ የጥንቱ ዓለም ባሕል ይንጸባረቃል። እግዚአብሔር ሙሴ ከግብፅ ያገኘውን እውቀት ሁሉ አምስቱን የመጀመሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት እንዲጽፍ በመርዳት ተጠቅሞበታል።

15ኛ ጥያቄ፤ ሀ) እግዚአብሔር በሕይወታችን ውስጥ የሚያጋጥሙንን ክስተቶች የምሥራቹን ቃል ለማዳረስ እንዴት ይጠቀምባቸዋል?

ለ) እግዚአብሔር በሕይወትህና በልምምድህ ውስጥ ተራ የሚመስሉትን ነገሮች እርሱን በበለጠ እንድታገለግለው፥ አንተን ለማዘጋጀት የተጠቀመባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

ሙሴ ዘፍጥረትን ለመጻፍ መረጃዎቹን ከየት እንዳገኛቸው አናውቅም። ብዙዎቹ ታሪኮች ከእስራኤላውያን በቃል ሲወርድ ሲዋረድ የመጡ ሊሆኑ ይችላሉ። ሌሎች ታሪኮችም በጽሑፍ ተዘግበው በተለያዩ ሰዎች የተጠበቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ሙሴ በትምህርት ቤት ሳለ ከግብጻውያን ቤተ መጻሕፍትም አንዳንዶቹን አንብቦ ሊሆን ይችላል። ሙሴ ስለተጠቀመባቸው ምንጮች እርግጠኞች ሆነን መናገር

ባንችልም፥ በሚጽፍበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንደመራውና ትክክለኛ ታሪኮችን እንደ ጻፈ እናውቃለን።

የዘፍጥረት መጽሐፍ ዋና ዓላማ

የስሙ ትርጉም እንደሚያመለክተው፥ ዘፍጥረት የነገሮች ሁሉ ጅማሬ መጽሐፍ ነው። ሙሴ በዘፍጥረት ውስጥ ያለ ጥርጥር ብዙ ታሪኮችን ሊጽፍ ቢችልም፥ እርሱ ግን የመጽሐፉን ዓላማዎች የሚያስጨብጡለትን ሁለት ፍሬ ነገሮች ብቻ መርጧል። መጀመሪያ፥ ሙሴ የእግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ ዓለም እንዴት እንደተፈጠረ እንዲያውቁ ፈልጓል። ሙሴ በመጽሐፉ የሚያተኩረው በሰዎች ጉብዝና ላይ ሳይሆን፥ በእግዚአብሔር ላይ ነው። እግዚአብሔር የታሪክ ሁሉ እምብርት ነው። እርሱ የሚታዩትንና የማይታዩትን ፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ ነው (ቆላስይስ 1፡16 ተመልከት)። ኃጢአት ወደ ዓለም የመጣው፥ በእግዚአብሔር ላይ ከተደረገ ዓመፅ ሳቢያ ነው። ዛሬ በዓለም ላይ ወደምንመለከታቸው ጦርነቶችና ክፋቶች የሚያመራውም ይኸው በእግዚአብሔር ላይ የሚደረገው የማያቋርጥ ዓመፅ ነው። ዳሩ ግን እግዚአብሔር ከኃጢአት የተነሣ የተበላሸውን ግንኙነት ለማደስ ያለማቋረጥ ሰውን እንደሚፈልግ አምላክ ሆኖ ተገልጾአል።

ሁለተኛ፥ ሙሴ በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት እስራኤላውያን እንዴት እንደተነሡ ለማሳየት ፈልጎ ነበር። እንደምታስታውሰው፥ ፔንታቱክ ሲጻፍ እስራኤላውያን ለአራት መቶ ዓመታት በግብፅ የባርነት ቀንበር ሥር ነበሩ። ማንነታቸውንና እግዚአብሔር እንደመረጣቸውም ረስተው፥ ወይም ተጠራጥረው እንደ ነበሩ አያጠያይቅም። የዘፍጥረት መጽሐፍ፥ ሕዝበ-እስራኤል እግዚአብሔር ከዓለም ሕዝቦች ከመረጠው ከአንድ ታማኝና ጻድቅ ሰው፥ ከአብርሃም፥ እንዴት እንደ ጀመሩ ያስተምራል። እርሱም በእግዚአብሔር ላይ ካለው እምነትና መታዘዝ የተነሣ አዲሱ የእስራኤል ሕዝብ ተጀመረ። አብርሃም እስራኤላውያን ሁሉ ሊመስሉት የሚገባው ፍጹም የእግዚአብሔር ሰው ሆኖ ተገልጾአል። አብርሃም የእምነትና የታዛዥነት ሕይወት የነበረው ሰው ነበረ። 16ኛ ጥያቄ፤ አይሁዶች ባንሆንም እንኳ፥ እነዚህ በአብርሃም ሕይወት ውስጥ የታዩት ሁለት

ባህሪያት፥ ዛሬ ለእኛም የሚያስፈልጉን እንዴት ነው? ጳውሎስ ስለ ብሉይ ኪዳን ሲጽፍ፥ «እነዚህም ክፉ ነገር እንደተመኙ፥ እኛ ደግሞ እንዳንመኝ ይህ ምሳሌ ሆነልን» (1 ቆሮ. 10፡6) ይላል። ዘፍጥረት፥ እግዚአብሔርን ለመታዘዝ በክርስትና ሕይወታችን እንዴት መመላለስ እንዳለብን በምሳሌነት ሊያስተምሩን የሚችሉ በርካታ ጥሩ ታሪኮችን አካቶ ይዟል። ደግሞም በኃጢአት ከተሞላ ሕይወትና ከውጤቶቹ እንድንርቅ የሚያስጠነቅቁን ታሪኮችም በዘፍጥረት ውስጥ ይገኛሉ። ዘፍጥረትን በምናጠናበት ጊዜ ስለ ዓለም አጀማመር ሐቁን ለማወቅ መጣር ብቻ ሳይሆን፥ በተጨማሪ እራሳችንን፥ «እግዚአብሔርን በማስደሰት ለመኖር ከታሪኮቹ ምን ለመማር እንችላለን?» ብለን መጠየቅ አለብን። እንደ አብርሃም እኛም «የእግዚአብሔር ወዳጅ» ተብለን ልንታወቅ ያስፈልጋል። 17ኛ ጥያቄ፤ ሀ) ከእዚህ ቀደም ከምታውቃቸው የዘፍጥረት ታሪኮች ውስጥ፥ ክርስቲያኖች እንዴት መኖር እንዳለባቸው መልካም ምሳሌዎች የሚሆኑ ሁለት ታሪኮችን ጻፍ። ለ) እንዲሁም ደግሞ ክርስቲያኖች እንዴት መኖር እንደ ሌለባቸው የሚያሳዩ ሁለት ምሳሌዎችን ጻፍ። ሦስተኛ ቀን

18ኛ ጥያቄ፤- ዘፍጥረት 25-35 አንብብ። የዘፍጥረትን መጽሐፍ አስተዋጽኦ ማውጣትህን ቀጥል።

የዘፍጥረት መጽሐፍ ጭብጥ

በዘፍጥረት መጽሐፍ ሁሉ «በረከት» እና «መርገም» የተባሉትን ሁለት ቃላት በተደጋጋሚ እናያለን (ዘፍ. 12፡1-3 ተመልከት)። እነዚህ ሁለቱ ቃላት የዘፍጥረትን መጽሐፍ ጭብጥ ይዘዋል። እግዚአብሔር ዓለምን ሲፈጥር መልካም ነበርና፥ ሁሉንም ነገር ባርኮአል። እንስሶች ተባርከዋል፤ ሰው ተባርኮዋል፤ ሰባተኛውም ቀን ተባርኮ ነበር። ሁሉም ፍጥረት «መልካም» ተብሎ ተጠርቶ ነበር። በኋላም ቀደምት አባቶችና መላው እስራኤል እንዴት በእግዚአብሔር እንደተባረኩ ዘፍጥረት ያሳያል።

የበረከቱ ተቃራኒ «መርገም» ወይም በኃጢአተኞች ላይ የሚመጣ ፍርድ ነው። ዘፍጥረት እግዚአብሔርን በማይታዘዙ ሰዎች ላይ የሚደርሱ በርካታ እርግማኖችንም ይዞአል። በመጀመሪያው ኃጢአት

ምክንያት አዳምና ሔዋን፥ ዓለም፥ ሰይጣን፥ ሁሉም ተረግመዋል። የመጀመሪያው ነፍሰ-ገዳይ ቃየን ተረግሟል። ሌሎችም በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት በመሥራታቸው ተረግመዋል።

ከበረከትና ከርግማን አሳብ ጋር ተያይዞ የመልካምና የክፉ አሳብም በቅዱሱ እግዚአብሔር ፊት ነው። እግዚአብሔር የፈጠረው በሙሉ መልካም፥ ቅዱስ፥ ፍጹምና እርሱን የሚያስከብር ነበር። እግዚአብሔር ከፈጠረው ሰው የሚፈልገው ብቸኛ ነገር ለሕግጋቱ መታዘዝን ነው። ከእግዚአብሔር በረከት የሚወጣው ለሕግጋቱ ከመታዘዛችን ውስጥ ነው።

ነገር ግን ከሰው ውድቀት የተነሣ ክፉት ደግነትን ዋጠው። የመጀመሪያው ኃጢአት እግዚአብሔር የፈጠረውን መልካሙን ዓለም አበላሸው። ወዲያውም ከኖኅና ቤተሰቦቹ በቀር፥ ሰዎች ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ በማመፃቸው በጥፋት ውኃ መደምሰስ ነበረባቸው። እንደ ዛሬው ክፉታችን ሁሉ፥ የጥንቱም ዓለም ክፋት፥ በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ውስጥ ያለውን መልካም ነገር ያጠፋል። ለእግዚአብሔር ርግማን መሠረቱ፥ ለትዕዛዛቱ አለመገዛት ነው። ዛሬም ቢሆን የእግዚአብሔርን ቁጣ ወደ ዓለም የሚያመጣው፥ ይህ ለትዕዛዙ አለመገዛት ነው።

19ኛ ጥያቄ፤ - ክፋት፥ የእግዚአብሔርን መልካም ነገር፥ ከሕይወትህ፥ ከቤተ ክርስቲያንና ከዓለም የሚያጠፋው እንዴት ነው?

20ኛ ጥያቄ፤ - ለአንድ ክርስቲያን በረከት ከመታዘዝ፥ መርገም ደግሞ ካለመታዘዝ እንደሚመጣ የምንነግረው በምን መንገድ ነው?

አብዛኛዎቹ የዘፍጥረት ታሪኮች፥ እንግዲህ፥ እግዚአብሔር የክፉውን ውጤቶች ለማጥፋት፥ ወይም ለመገደብ እንዴት እንደ ሠራ የሚያመለክቱ ታሪኮች ናቸው። ክፉ ሰዎችን ለማጥፋት የጥፋት ውኃ ላከባቸው። ለኃጢአት እንዳይተባበሩ በተናቸውና በመጨረሻም አብርሃምን መረጠ። በእርሱና በዘሩ የሚከተለውንና የሚታዘዘውን ሕዝብ ለመፍጠር ተለመ። የሚያሳዝነው ግን፥ በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች ሳይቀሩ በኃጢአት በመጠመዳቸው፥ በዓለም ሕዝቦች ፊት ጥሩ ምሳሌዎች ለመሆን አልበቁም።

አብዛኛዎቹ የዘፍጥረት ታሪኮች፥ እንግዲህ፥ እግዚአብሔር የክፉውን ውጤቶች ለማጥፋት፥ ወይም ለመገደብ እንዴት እንደ ሠራ የሚያመለክቱ ታሪኮች ናቸው። ክፉ ሰዎችን ለማጥፋት የጥፋት ውኃ ላከባቸው። ለኃጢአት እንዳይተባበሩ በተናቸውና በመጨረሻም አብርሃምን መረጠ። በእርሱና በዘሩ የሚከተለውንና የሚታዘዘውን ሕዝብ ለመፍጠር ተለመ። የሚያሳዝነው ግን፥ በእግዚአብሔር የተመረጡ ሕዝቦች ሳይቀሩ በኃጢአት በመጠመዳቸው፥ በዓለም ሕዝቦች ፊት ጥሩ ምሳሌዎች ለመሆን አልበቁም።

21ኛ ጥያቄ፤ - ክፋት በእግዚአብሔር ሕዝብና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አዘውትሮ የሚታየው እንዴት ነው?

ከዘፍጥረት መጽሐፍ የምንማራቸው ዋና ዋና ትምህርቶች

1. ዘፍጥረት የነገሮች ሁሉ ጅማሬ መጽሐፍ ነው። በተለይ በሰው አፈጣጠር ላይ በማተኮር የፍጥረትን መጀመሪያ ያሳያል። የቤተሰብን፥ የኃጢአትና የመቤዠትን፥ የመጀመሪያ ሕዝቦችን፥ የተለያዩ ቋንቋዎችን ጅማሬና በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር ሕዝቦች ሆነው የተመረጡትን የእስራኤላውያንን ጅማሬ ይናገራል። የዘፍጥረት ታሪክ ትኩረት በዓለም ላይ ስለሆነ፥ አንዳንድ ነገሮች እንዴት እንደተጀመሩ (ለምሳሌ፡- መላእክት፥ ሰይጣን ...) አይገልጽልንም። ሆኖም እግዚአብሔር የነገሮች ሁሉ ጅማሪ እንደሆነ እርግጠኞች እንድንሆን በቂ መረጃዎች ተሰጥተዋል።

2. ሰዎች በብዙ አማልክት በሚያምኑበት ዘመን ስለተጻፈ፥ ዘፍጥረት በአንዱ እውነተኛ አምላክ ላይ ያተኩራል። የእግዚአብሔርን ማንነት ለመግለጽ ባይሞክርም፥ ስለ እግዚአብሔር ከዘፍጥረት መጽሐፍ ብዙ ነገሮችን እንማራለን። አንዳንዶቹም የሚከተሉት ናቸው፡-

   ሀ. ብዙ ሳይሆን፥ አንድ አምላክ ብቻ አለ። ዘፍጥረት ብዙ አማልክት እንዳሉ አድርጎ የሚቀበለውን የአረማውያን አመለካከት በግልጽ ይቃወማል።

   ለ. እግዚአብሔር የፍጥረት ሁሉ ፈጣሪ ነው። እርሱ ብቻ አልተፈጠረም። በሰማይም ቢሆን በምድር እግዚአብሔር የሁሉ ምንጭና በሁሉም ላይ ገዥ ነው።

ሐ. እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ለመገናኘት ይፈልጋል። በዘፍጥረት ውስጥ አዳምን የፈጠረው፥ ለማነጋገርም የፈለገው እግዚአብሔር እንደሆነ እንመለከታለን። ከቃየንም ጋር የተገናኘው እግዚአብሔር ነበር። አብርሃምን የመረጠውም እርሱ ነበር። ከሰዎች ጋር ግንኙነት ለማድረግ የሚሻ አምላክ እንጂ፥ እንዲያው ባህሪይ-አልባ የሆነ ኃይል አይደለም።

መ. እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። እግዚአብሔር ኃጢአትን ሳይቀጣ አያልፍም።

ሠ. እግዚአብሔር መሐሪ ነው። እግዚአብሔር የሰውን ልጆች ኃጢአት ባደረጉ ጊዜ ሊያጠፋቸው ሲችል፥ ለኃጢአተኞች ምህረቱን አሳየ። እርሱ የደኅንነትን መንገድ ያዘጋጃል።

ረ. እግዚአብሔር አንድ ቢሆንም፥ እርሱ አንድ አካል ብቻ አይደለም። ስለ ሥላሴ ከዘፍጥረት አስረግጠን ለማስረዳት ባንችልም፥ እግዚአብሔር ከአንድ የበለጡ አካላት እንዳሉት የሚያመለክቱ ጥቅሶችን በተደጋጋሚ እናያለን።

22ኛ ጥያቄ፤ - እነዚህን እውነቶች የሚያስተምሩትን አንዳንድ ምሳሌዎች ከሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ጥቀስ።

3. በዘፍጥረት መጽሐፍ በእግዚአብሔር ዓላማዎች ውስጥ ለሰው የተሰጠውን ከፍተኛ ሥፍራ እናያለን። ሰው ብቻ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሮ፥ በፍጥረት ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጥቶታል። እግዚአብሔር ከሰው ጋር ኅብረት አድርጓል። ሰው በእዚአብሔር ላይ ኃጢአት ባደረገ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ሰው የሚድንበትን መንገድ አዘጋጅቷል። በዘፍጥረት መጽሐፍ፥ ሰው ከእግዚአብሔር ርቆ ወደ ጠሊቅ ኃጢአት ለመዘፈቅ ያለውን የማያቋርጥ መሻት እናያለን። አብርሃምና የእርሱ ልጆች ሳይቀሩ፥ የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝቦች ኃጢአተኞች ነበሩ። እግዚአብሔር ከእኛ ምን እንደሚፈልግብንም እንረዳለን - ለትዕዛዛቱ እንድንገዛና በዙሪያችን ካለው ክፉት በተቃራኒ ቅዱሳን እንድንሆንለት ይሻል።

3. በዘፍጥረት መጽሐፍ በእግዚአብሔር ዓላማዎች ውስጥ ለሰው የተሰጠውን ከፍተኛ ሥፍራ እናያለን። ሰው ብቻ በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጥሮ፥ በፍጥረት ሁሉ ላይ ሥልጣን ተሰጥቶታል። እግዚአብሔር ከሰው ጋር ኅብረት አድርጓል። ሰው በእዚአብሔር ላይ ኃጢአት ባደረገ ጊዜ፥ እግዚአብሔር ሰው የሚድንበትን መንገድ አዘጋጅቷል። በዘፍጥረት መጽሐፍ፥ ሰው ከእግዚአብሔር ርቆ ወደ ጠሊቅ ኃጢአት ለመዘፈቅ ያለውን የማያቋርጥ መሻት እናያለን። አብርሃምና የእርሱ ልጆች ሳይቀሩ፥ የእግዚአብሔር ምርጥ ሕዝቦች ኃጢአተኞች ነበሩ። እግዚአብሔር ከእኛ ምን እንደሚፈልግብንም እንረዳለን - ለትዕዛዛቱ እንድንገዛና በዙሪያችን ካለው ክፋት በተቃራኒ ቅዱሳን እንድንሆንለት ይሻል።

4. የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ በዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ኃጢአተኞችን ወደ ንስሃ ለመጥራት ያለ ማቋረጥ የሚፈልገው እግዚአብሔር ነው። የእግዚአብሔር ጸጋ የደኅንነት ምንጭ ሆኖ ታይቷል። አብርሃም እግዚአብሔር በሥራው እንዲመርጠው አልሞከረም። ይልቁንም እግዚአብሔር መረጠውና ከዚያም በኋላ እምነቱን እንደ ጽድቅ ቆጠረለት (ዘፍ. 15:6)።

5. የእግዚአብሔር በረከቶች በቃል ኪዳኑ ላይ የተመሠረቱ ናቸው። አዳምና ሔዋን በኃጢአት ከወደቁ በኋላ፥ የመጀመሪያውን የእግዚአብሔርን በረከት አጡ። ነገር ግን እግዚአብሔር ያንን በረከት ለማደስ ያለ ማቋረጥ ሠርቷል። ስለዚህ ከሰው ጋር የገባውን ቃል ኪዳን አደሰ። በአሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ቃል ኪዳኖች አሉ። እግዚአብሔር ለኖኅ የሰጠው ቃል ኪዳን (ዘፍ. 9:8-17)፥ እንደዚሁም እግዚአብሔር ከአብርሃም ጋር የገባው ቃል ኪዳን (ዘፍ. 15:9-21) አለ። በኋላም በሙሴ ጸሐፊነት በብሉይ ኪዳን እንደታየው፥ ከአብርሃም ጋር የተደረገው ቃል ኪዳን ዋና ዓላማ እስራኤልን የዓለምን ሕዝብ ሁሉ የመባረኪያ መንገድ ለማድረግ ነበር። የመጀመሪያዋን የዔደን ገነት በረከት መልሶ የሚያመጣበት

የእግዚአብሔር መሣሪያ የምትሆን እስራኤል ነበረች። ሆኖም እንደምናውቀው፥ ለቃል ኪዳኑ ባለመታዘዟ፥ እስራኤል ብቻ ሳትሆን፥ ሕዝቦች ሁሉ ቃል የተገባላቸውን በረከት አላገኙም። ይህም ነው በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ የተመሠረተው አዲሱ ቃል ኪዳን ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት።

23ኛ ጥያቄ፤- ሀ) እነዚህ እውነታዎች በሌሎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ውስጥ እንዴት እንደተገለጹ ምሳሌዎችን ስጥ።

ለ) ከእነዚህ ዋና ዋና ትምህርቶች፥ ከእግዚአብሔር ጋር ስላለን ግንኙነት ምን እንማራለን?

ሐ) እነዚህን እውነታዎች ክርስቲያኖች ሁሉ እንዲማሩዋቸው የሚያስፈልገው ለምንድነው? መ) ቤተ ክርስቲያንህ እነዚህን እውነቶች እንዴት እያስተማረች ነው?

አራተኛ ቀን

24ኛ ጥያቄ፤ ከዘፍጥረት 36-50 አንብብ። የዘፍጥረት መጽሐፍ አስተዋጽኦህን አጠናቅ።

የዘፍጥረት መጽሐፍ አወቃቀር

25ኛ ጥያቄ፤ ከኦሪት ዘፍጥረት መጽሐፍ ንባብህ እንደተረዳኸው፥ ሁለቱ የዘፍጥረት መጽሐፍ አበይት ክፍሎች ምንና ምን ይመስሉሃል?

ዘፍጥረት በሁለት አብይት ክፍሎች ይከፈላል። የመጀመሪያው ክፍል ዘፍ. 1-11 ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ ዘፍ. 12-50 ያለው ነው። እነዚህ ሁለት ክፍሎች በሚከተለው መንገድ ሊነጻጸሩ ይችላሉ፡-

1. የዘፍጥረት ታሪክ ከምዕራፍ 1-11 በዓለም አቀፍ ክስተቶች ላይ ያተኩራል። ይህንንም ስንል የግለሰቦች ታሪኮች ቢኖሩም፥ ትኩረቱ በዓለም አፈጣጠር፥ በዓለም ሕዝቦች አመሠራረት፥ በዓለም ሁሉ በተከሰተው የጥፋት ውኃ ላይ፥ ወዘተ. ነው ማለታችን ነው።

ከዘፍጥረት 12-50 ያለው በይበልጥ በአንድ ቤተሰብ ታሪክ ላይ የተወሰነ ሲሆን፥ ይህም የአብርሃም ቤተሰብ ነው።

2. የዘፍ. 1-11 ትኩረት ሰው ከፈጣሪው አምላክ እንዴት እየራቀ እንደሄደ በማሳየቱ ላይ ነው። የዘፍ. 12-50 ትኩረት ደግሞ እግዚአብሔር እንዴት ሰውን ከእርሱ ጋር ወዳለው ትክክለኛ ግንኙነት መልሶ እንዳመጣው በማመልከት ላይ ነው።

እነዚህ የዘፍጥረት ሁለት አበይት ክፍሎች እያንዳንዳቸው እንደሚከተልው በአራት ሊከፈሉ ይችላሉ፡-

1. ዘፍጥረት. 1-11- አራት ዋና ዋና ክስተቶች

ሀ. የነገሮች ሁሉ መፈጠር - ምዕራፍ 1-2

ለ. የሰው በኃጢአት መውደቅ - ምዕራፍ 3-5

ሐ. እግዚአብሔር ዓለምን የቀጣበት የጥፋት ውኃ - ምዕራፍ 6-9

መ. የባቢሎን ግንብና የሕዝቦች በዓለም መበተን - ምዕራፍ 10-11

ይህ ክፍል በይበልጥ ስለ ሰው ዘር ጅማሬ ይተርካል። ትረካው ምን ያህል ዓመታት እንደሚሸፍን ለማወቅ አይቻልም። አንዳንዶች ይህ ክፍል የሁለት ሺህ ዓመታት ታሪክ ይሸፍናል ይላሉ። ሌሎች ክርስቲያኖች ደግሞ ሃያ ሺህ ዓመታት ወይም ይበልጥ ይሸፍናል ይላሉ።

2. ዘፍጥረት 12-50 - አራት ዋና ዋና ሰዎች፡-

ሀ. አብርሃም - ምዕራፍ 12-23

ለ. ይስሐቅ - ምዕራፍ 24-26

ሐ. ያዕቆብ - ምዕራፍ 27-36

መ. ዮሴፍ - ምዕራፍ 37-50

ይህ ክፍል የዕብራውያንን ጅማሬ ከመናገሩም በላይ፥ በአንድ የአብርሃም ቤተሰብ ላይ ያተኩራል። ይህን የዘፍጥረት ታሪክ ክፍል ትክክለኛ ዘመን ለማስቀመጥ እንችላለን። የሦስት መቶ ስድሳ ዓመታት ታሪክ የሚሸፍን ነው። ይህ ክፍል የመጽሐፉን ከመቶ ሰማንያ እጅ የሚይዝና ጸሐፊውም በከፍተኛ ደረጃ ያተኮረበት ነው።

ይህ ከአንተ የዘፍጥረት አስተዋጽኦ ጽሑፍ ጋር እንዴት ይነጻጸራል? የዘፍጥረትን መጽሐፍ በምናጠናበት ጊዜ፥ እነዚህን ክፍሎች በአእምሮህ ያዝ።

በሁለተኛው የዘፍጥረት ክፍል፥ የእግዚአብሔርን የብሉይ ኪዳን ሦስት ዋና ዋና ዓላማዎች እናያለን። በመጀመሪያ የእግዚአብሔርን የአዳኝነት ዓላማ እናያለን። ይህንንም ኢየሱስ ክርስቶስ ከአብርሃምና ከአይሁዳዊ ዘሮቹ ከእነርሱ እንዲወለድ በመምረጡ እናያለን። ከአብርሃም የዘር ሐረግና በጎላም ከይሁዳ ነቢር የዓለም አዳኝ መምጣት የነበረበት።

ሁለተኛ፥ ከዘፍ. 12፡50 የአብርሃምን ቤተሰብ የነጋሢ ትውልድ አጀማመር እንመለከታለን። በምድር ሁሉ ላይ የሚገዛው መሢሕ የሚመጣው የአብርሃም ዘር ከሆነው ከይሁዳ ነበር።

ሦስተኛ፥ እግዚአብሔር የአብርሃምን ቤተሰብ የመረጠበትን የመገለጥ ዓላማ እንመለከታለን። በአብርሃምና በተመረጡት የአይሁድ ሕዝቦቹ በኩል ነበር እግዚአብሔር ቅዱስ ቃሉን ለዓለም የሚያስተላልፈው። የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች በሙሉ ለማለት ይቻላል አይሁዳውያን ነበሩ።

26ኛ ጥያቄ፤ - ሀ) እነዚህ ሦስት ዓላማዎች በአዲስ ኪዳን ውስጥ የተፈጸሙት እንዴት ነው?

ለ) ዛሬስ ለእኛ በረከት የሆኑት እንዴት ነው?

ሌላው የዘፍጥረትን መጽሐፍ አስተዋጽኦ ጽሑፍ የማዘጋጀ ምቹ መንገድ ‹ዘፍጥረት› (ጂነሲስ) በሚለው ርዕስ ዙሪያ ሲሆን፥ ትርጉሙም ‹መጀመሪያ› ማለት ነው፤ ይኸውም እንደሚከተለው ይታያል።

ምዕራፍ 1-2 - የዓለምና በውስጧ ያሉት ፍጥረታት ጅማሬ።

ምዕራፍ 3 - የኃጢአት ጅማሬና የመጀመሪያው የደኅንነት ተስፋ።

ምዕራፍ 4-9- የቤተሰብ ሕይወት፥ የሥልጣኔ፥ ወዘተ. ጅማሬ።

ምዕራፍ 10-11 - የዓለም ነገዶች ጅማሬ።

ምዕራፍ 12-50 - የአብርሃም ልጆች የሆኑት የአይሁድ ሕዝብ ጅማሬ።

የኦሪት ዘፍጥረት ብዙ ሊቃውንት የዘፍጥረትን መጽሐፍ አስተዋጽኦ የሚያወጡት «የ ... የትውልዱ መጽሐፍ ይህ ነው» ከሚለው የጸሐፊው ዓረፍተ ነገር ዙሪያ በመነሣት ነው። እንደዚህ ዓይነት አሥር ዓረፍተ ነገሮች ስለሚገኙ፥ እነርሱም የዘፍጥረትን መጽሐፍ በአሥር ዋና ዋና ክፍሎች ይከፍላሉ (ዘፍ. 2:4፤ 5:1፤ 6:9፤ 10:1፤ 11:10፤ 11:27፤ 25:12፤ 25:19፤ 36:1፤ 37:2)።

27ኛ ጥያቄ፡- ዘፍጥረት የተቀረውን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እንድንረዳ መሠረት የሚሆንባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

28ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ለመንፈሳዊ ሕይወትህ በጎነት የሚረዳ ከዘፍጥረት ምን ትምህርት የምታገኝ ይመስልሃል?

ለ) በዘፍጥረት ውስጥ የሚገኙት ታሪኮች፥ ከዚህ ቀደም ለመንፈሳዊ ሕይወትህ እገዛ ያደረጉት እንዴት ነበር?

አምስተኛ ቀን፡-

የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ዝግጅት እንዲረዱህ የሳምንታዊ ውይይት ጥያቄዎችን ተመልከት።

ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ - መሪው፥ በዚህ ሳምንት ከተከታተልነው ትምህርት አንድ አርዕስት ወይንም ጥቅስ በመውሰድ ከ5-10 ደቂቃዎች የሚወስድ የጽሞና መልእክት በማዘጋጀት ከተማሪዎቹ ጋር መካፈል አለበት።

2. ጸሎት - ለእያንዳንዳችሁና ለቤተ ክርስቲያን ስለሚያስፈልጓችሁ ነገሮች ለመጸለይ አሥር ደቂቃ ውሰዱ።

3. ክለሳ - የሳምንቱን ትምህርት ለአሥራ አምስት ደቂቃዎች ክለሱ። መምህሩም ትምህርቱን በትክክል ማጠናቀቃቸውንና መረዳታቸውን ለማወቅ፥ የእያንዳንዱን ተማሪ መልሶች ማረጋገጥ አለበት።

እያንዳንዱም ተማሪ ከዚህ ትምህርት ስላገኘው እውቀት መምህሩ ማስታወሻ መያዝ ይኖርበታል።

እንደዚሁም መሪው በዚህ ሳምንት ከተማሩት ውስጥ፥ ለተማሪዎቹ አጫጭር የሙከራ ጥያቄዎች ለመስጠት ይችላል።

4. ውይይት - በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩባቸው። ሁሉም አሳባቸውን መስጠታቸውን አረጋግጥ። እነዚህ ጥያቄዎች ከተማሪዎቹ ሕይወት ጋር በግልጽ መዛመዳቸውን አረጋግጥ።

ሀ. 1) በመጽሐፉ መግቢያ ላይ የተሰጡትን የመጽሐፍ ቅዱስ የግጥኛ ዘዴዎች መመሪያ ከልሱ።

2) ግንኙውንም የቅዱሳት መጽሐፍ ክፍል በምታጠናበት ጊዜ፥ እያንዳንዳቸውን አራት ዋና ዋና ጥያቄዎች፥ እንዴት መጠቀም እንደምትችል ምሳሌዎችን ስጥ።

3) እነዚህን አራት ነጥቦች አለመጠቀሙ፥ እንዴት ወደ ተሳሳቱ ትርጉሞች ሊያመራ እንደሚችል ምሳሌዎችን ስጥ።

4) ለተጠቀሱት ሦስት ዋና ዋና የሥነ - ጽሑፍ ዓይነቶች፥ ከዘፍጥረት ውስጥ ምሳሌዎችን ስጥ።

ለ. አስተዋጽኦዎቻችሁን አስተያዩ።

1)በምን መንገድ ይመሳሰላሉ?

2) እንዴት ይለያያሉ?

3) ለዘፍጥረት ይህንን አስተዋጽኦ ያወጣኸው ለምንድነው?

ሐ. የዘፍጥረት ዋና ዓላማ፥ እግዚአብሔር ዛሬም ከእኛ ጋር ለሚያደርገው ግንኙነት መሠረት ለመጣል ነው ለማለት የምንችለው በምን መንገድ ነው?

መ. ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን እንደሌላ ታሪክ ሳይሆን፥ ትክክለኛ፥ ስህተት የሌለበትና የእግዚአብሔር እስትንፋስ ውጤት የሆነ የእግዚአብሔር ቃል አድርገው መመልከት የሚያስፈልጋቸው ለምንድነው?

ሠ. 1. የአዳምና የሔዋን ክፋት የእግዚአብሔርን መልካም ሥራዎች በዛሬው ዓለማችን ውስጥ ጭምር አበላሽቷል ለማለት የምንችለው በምን መንገድ ነው?

2) ይህስ አብያተ ክርስቲያናታችንን እንዴት ይጎዳል?

3) ሕይወታችንንስ?

ረ. 1) እያንዳንዱ ተማሪ ከዚህ ቀደም የዘፍጥረት መጽሐፍ ለመንፈሳዊ እድገቱ እንዴት እንደረዳው ለቡድኑ አባላት ያካፍል።

2) እያንዳንዱ ተማሪ ከዘፍጥረት መጽሐፍ ውስጥ ለመማር ስለሚፈልጋቸው ነገሮች ለሌሎች ያካፍል።

5. ጸሎት - እግዚአብሔር የተማራችሁትን በተግባር እንድትፈጽሙ እንዲረዳችሁ በመጠየቅ ስብሰባውን በጸሎት ፈጽሙ።

ትምህርት ሁለት

ዘፍጥረት 1-2፡3

መጀመሪያ ቀን ዘፍጥረት 1፡1-2

1ኛ ጥያቄ፡- ሀ. የአዝጋሚ ለውጥ ሂደት ጽንሰ-አሳብ የዓለምን አጀማመርና ስለ ሁሉም ነገሮች፥ በተለይም ስለ ሰው አመጣጥ የሚያስተምረውን አጠር ባለ ጽሑፍ አቅርብ።

ለ. ክርስቲያኖች በትምህርት ቤት፥ እግዚአብሔር ዓለምን እንደፈጠረ ያላቸውን እምነት ለመከላከል ያስቸግራቸዋልን? ስለ አዝጋሚ ለውጥ ጽንሰ- አሳብስ የሚሰጡት ምላሽ እንዴት ነው?

ሁላችንም ስለ አዝጋሚ ለውጥ ጽንሰ-አሳብ በትምህርት ቤታችን ተምረናል። ይህም የሆነበት ምክንያት ዛሬ ሳይንስ የሚያተኩርበት ዋና ጽንሰ-አሳብ በመሆኑ ነው። የአዝጋሚ ለውጥ ጽንሰ-አሳብ ብዙ አመለካከቶች ቢኖሩትም፥ አንድ የወል የሆነ ትምህርት ግን አለው። ዛሬ የምናያቸው ሕይወቶች ሁሉ፥ ነገሮች ወደ በለጠና ከፍ ወዳለ